**የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር**
**(ኢብአግ)**

**Ethiopian National United Front**
**(ENUF)**

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
# ጋዜጣዊ መግለጫ

## ግንቦት ፲፩ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ የተፋው የሻዕቢያዊ/ወያኔ አምባገነን አገዛዝ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. እትም መሠረት የሌለው የሀሰት ውንጀላና ፕሮፓጋንዳ በመጠቀም በዶ/ር ቅጣው እጅጉ ተመሥርቶ ሲመራ በቆየው በኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢብአግ) እና አባላት ላይ ክስ መሥርቻለሁ ማለቱ ይታወሳል። ወያኔ/ኢሕአዴግ እነዚህን ዜጎች ከሁለት ዓመታት በላይ በቃሊቲ እስር ቤት አጉሮ ሲያሰቃይ ቆይቶ ይኸው ዛሬ 55 የኢብአግ አባላት ናቸው ባላቸው ዴሞክራቶች ላይ ከአንድ እስከ አስራ አምስት ዓመት በእስራት እንዲሰቃዩ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕገ-መንግሥት በጣሰ መልኩ አስፈርዶባቸዋል።

በአቶ መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ የሚመራው ሕገ-ወጥ፣ ዘረኛና ሽብርተኛ አገዛዝ፣ የአሜሪካን ናሳ የጠፍር መንኰራኩር ተመራማሪ ሳይንቲስት የነበረው ገናናው የኢትዮጵያ አርበኛ እንጅነር ዶ/ር ቅጣው እጅጉ ከስምንት ዓመት በፊት መሥርቶ እስከ ዕለተ እረፍቱ ሲመራ የቆየው ኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢብአግ) ዛሬም የመሥራቹን ራዕይ በመከተልና የድርጅቱን አርማ በማንገብ በኢትዮጵያ ውስጥና በዓለም ዙሪያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲመሠረት ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ላይ ይገኛል። ወደፊትም ትግሉ ይቀጥላል።

ወያኔ ትላንትም፣ ዛሬም በጦር መሣሪያ ኃይል የኢትዮጵያን ሕዝብ በትረ-መንግሥት ጨብጦ፣ ሕጋዊ መሠረት በሌለው አገዛዝ ሕዝቡን በጎሳ ክልል ከፋፍሎ ሲያባላ ቆይቷል። ወያኔ/ኢሕአዴግ በሕዝብ ግፊት ተገዶና ለምዕራባውያን እይታና ድለላ ባወጣው የሕዝብ ተወካዮች የምርጫ ሥርዓት መሠረት በወርሃ ግንቦት ከተሸነፈ በኋላ፣ ሽንፈቱን አልቀበልም ብሎ ሰላማዊ ዜጎችን በአጋዚ ሰራዊት ማስፈጀቱና ወደ መቶ ሺ የሚደርሱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትን ወደ አፍሪቃዊ ጓንታናሞ አግዞ እስከ ዛሬ ድረስ አፍኖ ማሰቃየቱን የኢትዮጵያና የዓለም ሕዝቦች ያውቁታል። በመሆኑም ይህን አሰቃቂ የሰው ዘር ማጥፋት ዘመቻ ለመቋቋም የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና ጄኖሳይድ ዋች (Genocide Watch) በአቶ መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ላይ የሰው ዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ እንዲመሠረት ጠይቀዋል።

ይህ እንዲህ እንዳለ፣ ወያኔ/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአናሳ ጎሣ የጭቆና ቀንበር ጠምጄ ለዘለቄታው እነዳዋለሁ ብሎ ያወጣውን ዕቅድ እውን ለማድረግ፣ ኢ-ሕጋዊ የሆኑ የሽብር ዘዴዎችን ያለሃፍረት በመጠቀም፣ ሠላማዊውን አርሶ አደር፣ ተማሪ፣ ምሁር፣ ነጋዴ፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ከፍተኛ የጦር አዛዦች ለቅሞ በማሰርና በማጉላላት ላይ ይገኛል። ወያኔ/ኢሕአዴግ የኢብአግ አባላት ባላቸው ዜጎች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ መውሰዱ ባያስደንቀንም፣ ኢብአግ እነዚህ ንፁሃን ዜጎች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲመሠረት ያደረጉትን ተጋድሎ እያደነቀ፣ ድርጅታችንም ይሁን አባላቱ በማንኛውም ወቅት የትጥቅ አመጽ አራምደው እንደማያውቁ ያረጋግጣል። ይልቁንም በተጨባጭ መረጃ የትጥቅና የሽብር አራማጅ ነው ብሎ የኢትዮጵያና የዓለም ሕዝብ የዘገበው ወያኔያዊው ዘረኛ ድርጅት ሕወሓት ነው።



P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A.•
www.enufforethiopia.net

**ሆኖም፣ የእንተቴን ለእንተቴ እንዲሉ አቶ መለስና ግብረ አበሮቹ ከሁለት ዓመታት በፊት በድርጅታችን ላይ በሃሰትና በቅጥፈት የሰነዘሩት ውንጀላና ክስ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል።**

## የወያኔ ቅጥፈትና ክስ

3በመንግሥት ላይ የትጥቅ አመጽ ለማራመድ ተንቀሳቅሰዋል በተባሉ ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ ተመሠረተ
አዲስ አበባ - የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የትጥቅ አመጽ ለማራመድ ተንቀሳቅሰዋል ባላቸው 55 ሰዎች ላይ ትናንት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ መሠረተ::

ዓቃቤ ሕግ ክሱን የመሠረተው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የፖለቲካ ፓርቲ እና መሥራች ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች በመሆን ሲንቀሳቀሱ ከቆዩ በኋላ የግንቦት 97 ምርጫን ምክንያት በማድረግ በሕገ መንግሥት በተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የትጥቅ አመጽ ለማራመድ ተንቀሳቅሰዋል ባላቸው ግለሰቦች ላይ ነው::

ከተከሳሾቹ መካከልም 37ቱ በዕለቱ በሁለተኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው ዓቃቤ ሕግ የመሠረተባቸው ክስና የማስረጃ ዝርዝር እንዲደርሳቸው ተደርጓል::

የግንቦት 97 ዓ.ም የአገራዊ ምርጫን ውጤት መታወቅን ተከትሎ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የፖለቲካ ድርጅት መሥራች አባል ድርጅቶች ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል የማፍረስ ሙከራ ወንጀል በሕቡዕ እና በትጥቅ በተደገፈ አመጽ ለመቀጠል አቅደው ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በሚች ቅጣው እጅጉ መሪነት ከኢትዮጵያ ውጭ ቡድኑ መመሥረቱን የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ ካቀረበው ክስ ለመረዳት ተችሏል::

የሕቡዕ ድርጅቱ የአመራር አባላት ነን በሚሉ ነዋሪነታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ አሜሪካ እና ጀርመን በሆኑት መሥፍን ኃይሌ እና ለጊዜው ትክክለኛ ስማቸው እና የአባታቸው ስም በውል ባልተረጋገጠው አበበ፣ እንደሻው፣ ለምለም፣ ሣምሶን፣ ፋሲካ፣ አለሙ በተባሉት ግለሰቦችና ወኪሎቻቸው አማካይነት ተመልምለው ለተደራጁት የአሁኑ ተከሳሾች ቀጥታ የስልክ ግንኙነት ያደርጉ እንደነበር ተመልክቷል::

ተከሳሾቹ ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በሚሰጣቸው አመራር፣ ገንዘብና ተንቀሳቃሽ -ሞባይል? ስልክ እየታገዙ ከነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ እጃቸው እስከተያዘበት ታኅሣሥ ወር 1999 ዓ.ም በአዲስ አበባ፣ በደቡብና በአማራ ክልሎች የተለያዩ ከተሞች ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ እንደነበሩ ዓቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ አብራርቷል::

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ዓቃቤ ሕግ በግለሰቦቹ ላይ የመሠረተውን ክስና የማስረጃ ዝርዝር በዕለቱ እንዲደርሳቸው ተደርጓል:: ለተከሳሾቹ ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የክስ ቻርጁ የሚነበብላቸው መሆኑን ችሎቱ በመግለጽ እስከ ቀነ ቀጠሮው ባለው ጊዜ ተጠርጣሪዎቹ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ትዕዛዝ ሰጥቷል::4



P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A.•
www.enufforethiopia.net

ከዚህ በላይ የተነበበው የወያኔ መሠረተ ቢስ ውንጀላና ክስ መነሾ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየአለበት በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ሁለገብ ትግል (ሁለገብ ትግል ሳይንቲስት ቅጣው እጅጉ የተለመው የኢብአግ ዘይቤ ነው፣) በወያኔ አገዛዝ ላይ የሚሰነዝረውን የአመፅ ማዕበል ዘወትር በማሰብ፣ በመፍራትና በስጋት ተወጥሮ ወያኔ የረጨው ፕሮፖጋንዳ ከመሆን አያልፍም።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር የተመሠረተው በነሐሴ ወር ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. (ማለትም ከስምንት ዓመት በፊት፤) ሲሆን፣ በአሜሪካን መንግሥት ሕግ መሠረት በኅዳር ወር ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. ተመዝግቦና እውቅና አግኝቶ የሚንቀሳቀስ ሕጋዊ ድርጅት ነው። ኢብአግ የወያኔን ሕገ ወጥ አስተዳደር የአማጽያን አገዛዝና የሕወሓት የተራ ውንብድና ሥርዓትና ጥራዝ ነጠቅ የኮሚኒስት ማኒፌስቶና አፋኝ የዘረኞች አስተዳደር መሆኑን አጥብቆ ስለተገነዘበ፣ መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ይመኛሉ ብሎ አያምንም። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ ይቻላል ብሎ ማመኑ ጉም ለመጨበጥ መሞከር መሆኑን በመላው ሕዝብና በንጹሃን አባላቱ ላይ የደረሰው ግፍ ተጨባጭ ማስረጃ ነው።

ኢብአግ በመጽሔት፣ በድረገጽ፣ በጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ በድርጅቱ 3የሕዝብ ድምጽ ሬድዮ4፣ በሕዝባዊ ስብሰባዎችና በሲዲ (CD) የድርጅቱን ዓላማና የፖለቲካ ስልት በጠራ መልኩ ለሕዝብ አስተላልፏል። እንጅነር ዶ/ር ቅጣው እጅጉ ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት በጥቅምት ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. አትላንታ፣ ጆርጅያ፣ ሰሜን አሜሪካ ያደረጉት ንግግር ተቀድቶና CD ላይ ተቀርፆ በኢትዮጵያና በቀረው ዓለም ዙሪያ በመሰራጨቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢብአግ ዓላማ እና ግብ ምን እንደሆነ በሚገባ ተረድቷል። በመሆኑም ማንኛውም የወያኔ ውንጀላና የስም ማጥፋት ዘመቻ ድርጅታችንን ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ሊያዘናጋ ፈጽሞ አይችልም። እነዚህን መረጃዎች ከኢብአግ ድረገጽ ላይ http://www.enufforethiopia.net ማግኘት ይቻላል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ግብ ዓላማና ፕሮግራም ግልጽ ሆኖ ሳለ፣ ድርጅቱ የሚያካሂደው የትግል ስልት ሁለገብ ነው። ይህም ማለት በፀሎት፣ በሰላማዊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፣ በዲፕሎማቲክ ግንኙነት፣ በሙያና በማሕበረሰብ ትብብር፣ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወያኔ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የጦር መሣሪያ ሲመዝና ሲያጠቃ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት የመከላከል እርምጃዎችን ያጠቃልላል።

ሚያዚያ ፴ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም. ቁጥራቸው በግምት ፺፮ የሚሆኑ ሰላማዊ ወገኖቻችንን ከላይ የተዘረዘሩትን የፈጠራ ክሶች መሠረት በማድረግ የወያኔ ፍርድ ቤት በማንአለብኝነት ከሶስት እስከ ፲፮ ዓመት የእስራት ፍርድ ሰጥቻለሁ በማለት ታስረው እንዲገላቱና እንዲሞቱ ፈርዶባቸዋል።

ኢብአግ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ በወርሃ ግንቦት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በቆራጥ ሰላማዊ ትግል ተንቀሳቅሰው፣ በሕዝብ ተደግፈው፣ ጥቂቶችም መስዋዕት ሆነው፣ ለመላው ዓለም የዴሞክራሲ ጮራ ያበሰሩትን ድርጅቶች እያደነቀ፣ የድርጅቶቹ አመራሮችና አባላትም የሕዝብን ድምጽ አናሰርቅም በማለት ያደረጉትን የጀብድ ሰላማዊ ትግል እያከበረ፣ የሕዝብን የዴሞክራሲ ፍላጎትና እምነት ለማዳፈን የወንጀለኛው



P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A.•
www.enufforethiopia.net

የሻዕቢያዊ/ወያኔ አመራር አባላት መለስ ዜናዊ፣ አባይ ፀሓዬ፣ ስብሃት ነጋ፣ በረከት ስምዖን፣ ስዩም መስፍን፣ እንድርያስ እሸቴና ተላላኪዎች የፈፀሙትንና አሁንም በማካሄድ ላይ ያለውን ሕገ ወጥ የሰብአዊ መብት ገፈፋና ግድያ አጥብቆ ይቃወማል። ለወያኔ የግፍ አገዛዝ ሰለባ የሆኑትን ዜጎችም ይህ ሙሶሎኒአዊ የግፍና የሰቆቃ ሰዓት እስኪያልፍ እግዚአብሔር በየአሉበት እንዲጠብቃቸው እንማፀናለን።

በመጨረሻም ወያኔ በኢብአግ ላይ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ መክፈቱን በአሜሪካን ድምጽ ሬድዮ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በተላለፈው ዜና ከሰማን በኋላ ሁለት በዝግጅቱ ክፍል የታወቁ ጋዜጠኞችን በስልክና በኢንተርኔት አግኝተን በሬድዮ ዘጋቢያቸው ስለተላለፈው የሀሰት ክስ ምላሽ እንድንሰጥ እድል እንዲሰጠን በተደጋጋሚ ብንጠይቅም እድሉ ስለተነፈገን በወቅቱ ቅሬታችንን አሰምተን ነበር። አሁንም የአሜሪካን ድምጽ ሬድዮ አዘጋጆች የኢብአግን አመራር ስለዚሁ ጉዳይ ለማነጋገር ፈቃደኛ ካለመሆን አልፈው፣ በግፍ የታሰሩት ዜጎች ከሰላማዊ ትግል ውጭ ሌላ አማራጭ የለም ብሎ ሲከራከር የነበረ ድርጅት አባላት ናቸው በማለት የድርጅታችንንና የመስራች መሪአችንን ራዕይና ስም ለማጉደፍ ያቀዱትን በተግባር አሳይተዋል። በድጋሜ ከዚህ አድሎአዊ ሂደት እንዲቆጠቡ እያሳሰብን፣ የተሰማንን ቅሬታ ሕዝብ እንዲያውቅልና ታሪክ እንዲዘግብልን ጠቅሰን እናልፋለን። የቀሩት የዜና አገልግሎት ድርጅቶች እስከ አሁን ላደረጉልንና ወደፊትም ለሚያደርጉት ትብብር ከልብ እናመሰግናለን።

የመጨረሻው ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሆናል።
የወያኔ ዘረኞች የሙሶሎኒና የሂትለር እጣ ይጠብቃቸዋል።
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
ማዕከላዊ አመራር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ
ዋሽንግተን ዲሲ

ግንቦት ፲፩ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.



P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A.•
www.enufforethiopia.net